**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**
**የቤተሰብ ችሎት**
**የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ቅርንጫፍ**

______________________________
ስምዎን ያትሙ

______________________________
የመንገድ አድራሻ

______________________________
ከተማ፣ ግዛት እና ዚፕኮድ

☐ ተለዋጭ አድራሻ፡- ወከባ እና ጉዳት ይደርስብኛል ብለው በመፍራት የሌላ ሰውን አድራሻ ያስገቡ ከሆነ ሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ።

_______DRB _________________

ዳኛ፡- _____________________

ከሳሽ፣
ከ.

______________________________
የባለቤትዎን ስም ያትሙ

______________________________
የመንገድ አድራሻ

______________________________
ከተማ፣ ግዛት እና ዚፕ ኮድ

ተከሳሽ

**ለፍርድ ቤት የሚቀርብ የፍቺ ጥያቄ**
**የልጅ ማሳደጊያ ቀለብ ጥያቄ አለ** ☐ አዎ ☐ አይ

እኔ፣______________________________፣በዚህ የክስ መዝገብ ላይ ከሳሽ ስሆን እና የሚከተለውን ቃሌን እሰጣለሁኝ
ስምዎን ያትሙ

**1. ፍርድ ቤቱ ያቀረብኩትን ሕጋዊ የፍቺ ጥያቄ እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ለመወሰን ትክክለኛ የሆነ ቦታ የመሆኑ ምክንያት፡-** [ሁሉንም የሚመለከተው መልስ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ይሄንን ጥያቄ ለፍርድ ቤት ከማቅረቤ በፊት ከስድስት ወራት በላይ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ነዋሪ ነበርኩኝ።

☐ ይሄንን ጥያቄ ለፍርድ ቤት ከማቅረቤ በፊት ባለቤቴ ከስድስት ወራት በላይ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ነዋሪ ነበረ/ች።

2. **ባለቤቴ እና እኔ ተጋብተን የነበረው** [(አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ በሠርግ በ________________________________፣በ                         ውስጥ ነው።
ቀን                         ከተማ እና ግዛት

☐ ጋብቻ ሳይፈጸም አብሮ መኖር በ ወይም ________ገደማ፣ በ
______________________________________________________________________ ውስጥ ነው።
ቀን                         ከተማ እና ግዛት

ቀን

3. **ያለ በፍርድ ቤት የጸደቀ የጋብቻ ፍቺ ለብቻዬ ለመኖር እፈልጋለሁ።**

**[የተተወ ክፍል]**

4. **ስለ ጋብቻ ስሜ የሚከተለውን መግለጽ እወዳለሁ፦** (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ)

☐ ባለቤቴን ሳገባ ጊዜ ስሜን አልቀየርኩኝም።

☐ ባለቤቴን ሳገባ ጊዜ ስሜን ቀይሬአለሁኝ። ወደ ቀድሞ ስሜ መመለስ አልፈልግም።

☐ ባለቤቴን ሳገባ ጊዜ ስሜን ቀይሬ ነበር እና አሁን ስወለድ የተሰጠኝ ስም ወይም ሌላ ሕጋዊ ስም ላይ ለመመለስ እፈልጋለሁኝ። ይሄንን ጥያቄ ሳቀርብ ምንም ዓይነት ሕገወጥ ወይም የማጭበርበር ምክንያት የለኝም። እንዲመለስልኝ የምፈልገው የቀድሞ ስሜ፦

______________________________________________________________________
ፍርድ ቤቱ መልሶ እንዲያጸድቀው የሚፈልጉትን ስም ያትሙ

## በጋብቻ የተገኘ ንብረት እና ዕዳ

5. **በጋብቻዬ ስለተገኘው ንብረት የሚከተሉትን መግለጽ እፈልጋለሁ፦** (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ)

☐ ባለቤቴ እና እኔ በጋብቻ የተገኘ ምንም ንብረት የለንም።

☐ እኔ እና ባለቤቴ ሁሉንም የእኛን በጋብቻ የተገኘ ንብረት ጉዳዮች የሚፈታ ስምምነት አድርገናል እና ፍርድ ቤቱ እንዲያከፋፍለን ወይም የሀብት ክፍፍሉን እንዲወስንልን እየጠየኩኝ አይደለም።

☐ እኔ እና ባለቤቴ ሁሉንም የእኛን በጋብቻ የተገኘ ንብረት ጉዳዮች የሚፈታ ስምምነት አድርገናል እና ፍርድ ቤቱ ስምምነታችንን የፍርድ ቤት ማዘዣ ውስጥ እንዲያካትትልን እየጠየኩኝ ነው።

☐ እኔ እና ባለቤቴ ፍርድ ቤቱ ቤቱ እንዲያከፋፍለን ወይም ክፍፍሉን እንዲፈርድልን የምንጠይቀይበት በጋብቻ የተገኘ ንብረት አለን፣ እና ከዚህ ጥያቄ ጋር የማካትተው፣ አባሪ ሀ ላይ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች በመሙላት አባሪ አድርጌአለሁኝ።

☐ እኔ እና ባለቤቴ በጋብቻ የተገኘ ንብረት እንዳለን እና እንደሌለን እርግጠኛ አይደለሁም።

6. **በጋብቻዬ ላይ ስለተገኘው ዕዳ የሚከተሉትን መግለጽ እፈልጋለሁ፦** (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ)

☐ ባለቤቴ እና እኔ በጋብቻ የተገኘ ምንም ዕዳ የለንም።

☐ እኔ እና ባለቤቴ ሁሉንም የእኛን በጋብቻ የተገኘ ዕዳ ጉዳዮች የሚፈታ ስምምነት አድርገናል እና ፍርድ ቤቱ የዕዳ ድርሻ መጠናችንን እንዲወስንልን ሃላፊነት እንዲወስድ እየጠየኩኝ አይደለም።

☐ እኔ እና ባለቤቴ ሁሉንም የእኛን በጋብቻ የተገኘ ዕዳ ጉዳዮች የሚፈታ የጽሁፍ ስምምነት አድርገናል እና ፍርድ ቤቱ ስምምነታችንን የፍርድ ቤት ማዘዣ ውስጥ እንዲያካትትልን እየጠየኩኝ ነው።

☐ እኔ እና ባለቤቴ ፍርድ ቤቱ የዕዳ ድርሻችንን እንዲወስንልን የምንጠይቀይበት በጋብቻ የተገኘ ዕዳ አለን፣ እና ከዚህ ጥያቄ ጋር የማካትተው፣ አባሪ ሀ ላይ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች በመሙላት አባሪ አድርጌአለሁ።

☐ እኔ እና ባለቤቴ በጋብቻ የተገኘ ዕዳ እንዳለን እና እንደሌለን እርግጠኛ አይደለሁም።

## ቀለብ የመስጠት ሁኔታ

7. **ስለ ቀለብ የመሰጠት ሁኔታ ፍላጎቴ የሚከተሉትን መግለጽ እፈልጋለሁ፦** (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ)

☐ በቋሚነት እና ወይም በጊዜያዊነት ከባለቤት ቀለብ እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁኝ እና ባለቤቴ ለእኔ ቀለብ የመስጠት አቅም እንዳለው አምናለሁኝ።

☐ ጊዜያዊ የቀለብ ተቆራጭ አቤቱታ አቀርባለሁ (በክስ መዝገቡ ላይ ድጋፍ ለማግኘት)

☐ ባለቤቴ ለእኔ ቀለብ እንዲሰጠኝ አልፈልግም።

## የልጅ አሳዳጊነት መብት ሁኔታ

8. **ዕድሚያቸው ከ 18 ዓመት በታች ስለሆኑት ልጆቻችን የሚከተለውን እገልፃለሁ፦** (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ)

☐ ባለቤቴ እና እኔ ዕድሚያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ በጋራ ያፈራናቸው ልጆች (በወሊድ ሆነ

በጉዲፈቻ) የሉንም።

☐ ባለቤቴ እና እኔ ዕድሚያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ በጋራ ያፈራናቸው ልጆች (በወሊድ ሆነ በጉዲፈቻ) አሉን፣ ፍርድ ቤቱ በዚህ ጊዜ ላይ ስለአሳዳሪነት እና ሞግዚትነት እንዲፈርድልን አየጠየኩኝ አይደለም።

☐ ባለቤቴ እና እኔ ዕድሚያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ በጋራ ያፈራናቸው ልጆች (በወሊድ ሆነ በጉዲፈቻ) አሉን፣ እና ስለ አሳዳሪነትና ሞግዚትነት የጽሁፍ ስምምነት አለን እና ፍርድ ቤቱ በዚህ ጊዜ ላይ ስለአሳዳሪነት እና ሞግዚትነት እንዲፈርድልን አየጠየኩኝ አይደለም።

☐ ባለቤቴ እና እኔ ዕድሚያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ በጋራ ያፈራናቸው ልጆች (በወሊድ ሆነ በጉዲፈቻ) አሉን፣ ፍርድ ቤቱ ስለአሳዳሪነት እና ሞግዚትነት እንዲፈርድልን እጠይቃለሁ። ከዚህ ጥያቄ ጋር አያያዤ ያቀርብኩት፣ አባሪ ለ ላይ የሚያስፈልገውን መረጃ ሞልቼ ዓባሪ አድርጌአለሁ።

## የልጅ ማሳደጊያ የገንዘብ ድጋፍ

**9. የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ ገንዘብ በተመለከተ የሚከተለውን እጠቅሳለሁ፦** (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ)

☐ ባለቤቴ እና እኔ በጋራ ያፈራናቸው ልጆች (በወሊድ ሆነ በጉዲፈቻ) የሉንም ወይም ዕድሚያቸው ከ 21 ዓመት በላይ እና አካለ ስንኩልነት ያለባቸው ለአካለ መጠን የደረሱ ልጆች አይደሉም።

☐ ባለቤቴ እና እኔ ዕድሚያቸው ከ 21 ዓመት በታች የሆኑ ወይም ለአካለ መጠን የደረሱ አካለስንኩላን የሆኑ በጋራ ያፈራናቸው ልጆች (በወሊድ ሆነ በጉዲፈቻ) አሉን፣ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ በዚህ ጊዜ ላይ የልጅ ማሳደጊያ ገንዘብ እንዲቆርጥልኝ አየጠየኩኝ አይደለም።

☐ ባለቤቴ እና እኔ ዕድሚያቸው ከ 21 ዓመት በታች የሆኑ ወይም ለአካለ መጠን የደረሱ አካለስንኩላን የሆኑ በጋራ ያፈራናቸው ልጆች (በወሊድ ሆነ በጉዲፈቻ) አሉን፣ እና የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ ገንዘብ በተመለከተ ስምምነት አለን፣ ይሄ ስምምነት በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ ገንዘብ መመሪያ ጋር አብሮ የሚሄድ እና/ወይም ፍትሃዊ እና ትክክል ነው።

☐ ባለቤቴ እና እኔ ዕድሚያቸው ከ 21 ዓመት በታች የሆኑ ወይም ለአካለ መጠን የደረሱ አካለስንኩላን የሆኑ በጋራ ያፈራናቸው ልጆች (በወሊድ ሆነ በጉዲፈቻ) አሉን፣ እና ፍርድ ቤቱ የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ እንዲፈርድልኝ እየጠየኩኝ ነው፣ ጰና ከዚህ መዝገብ ጋር በማያያዝ፣ አባሪ ሐ ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን አባሪ አድርጌአለሁ።

## አባሪዎች

**10. የሚከተለውን(ሉትን) አባሪ(አባሪዎች) አካትቼአለሁ፦** [ሁሉንም የሚመለከተው መልስ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ አባሪዎች የሉም
☐ አባሪ ሀ (በጋብቻ የተገኘ ሀብት እና/ወይም የጋብቻ ዕዳ)
☐ አባሪ ለ (የልጅ አሳዳሪነትና ሞግዚትነት)
☐ አባሪ ሐ (የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ ገንዘብ)

**11.** ልክ እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ጥያቄ ወይም ክስ መዝገብን የሚያካትት በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ሆነ ወይም በማንኛውም ሌሎች ግዛቶች ውስጥ እንዳለ አውቃለሁ ☐ / አላውቅም ☐ ። እባክዎ ተመሳሳይ ጥያቄ ወይም ጫብጥ የያዙትን ግዛት፣ ፍርድ ቤት እና ክስ መዝገብ ቁጥሮች ይዘርዝሩ።

| ፍርድ ቤት | የመዝገብ ቁጥር | የክሱ ዓይነት |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

## የእፎይታ ጥያቄ

**እኔ ፍርድ ቤቱ ሕጋዊ የጋብቻ ፍቺ ውሳኔ እንዲያጸድቅልኝ በአክብሮት እየጠየኩኝ ነው እና**
[የሚመለከተው መልስ ላይ ሁሉ ምልክት ያድርጉ]

☐ ፍትሃዊ፣ ትክክል እና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ በጋብቻ የተገኘውን ሃብታችንን እና/ወይም ዕዳችንን እንዲያከፋፍለን።

☐ ፍትሃዊ እና ትክክል በመሆነ መልኩ የቀለብ እና የሚከተሉት እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁኝ፦ [ሁሉም የሚመለከተው ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ጊዜያዊ የቀለብ መስጠት

☐ ቋሚ የቀለብ መስጠት

☐ ለልጁ(ጆቹ) ጥቅም በሚመች መልኩ የአሳዳሪነትና ሞግዚትነት መብት እንዲሰጠኝ።

☐ ይሄንን ክስ መዝገብ ባቀረብኩኝ 45 ቀናት ጊዜ ውስጥ የልጅ ማሳደግያ ተቆራጭ ገንዘብ ጥያቄ ላይ ሰሚ ችሎት እንዲዘጋጅልኝ እና ችሎቱ የሚሰማበት ቀን እና ሰዓት ለሌላኛው ወላጅ ለሰሚ ችሎት ፍርድ ቤት እንዲገኝ ማዘዣ ("NOHODA") እንዲሰጥልኝ እጠይቃለሁኝ።

☐ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ ገንዘብ መመሪያ እና በሌሎች ተግባራዊ የሚደረጉ ሕጎች መሰረት የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ ገንዘብ የሚከተሉትን ጨምሮ እንዲፈረድልኝ፣ [ሁሉም የሚመለከተው ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ የአሁን የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ ገንዘብ (ተቆራጩ ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊቱ የሚቀጥል)

☐ የኋሊት የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ ገንዘብ (ከዛሬ በፊት ለነበረው ጊዜ ተቆራጭ)

☐ የሕክምና ድጋፍ

☐ የጽሁፍ ስምምነት እንዳለን እንዲገነዘብ። ፍርድቤቱ የሚከተለውን እንዲያደርግልኝ እጠይቃለሁኝ፦ [አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ስምምነታችንን የዚህ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አካል በማድረግ *እንዲያካትትልኝ።*

☐ ስምምነታችንን የዚህ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አካል በማድረግ *እንዲያካትትልኝ፡፡*

☐ የቀድሞ ስሜ እንዲመለስልኝ።

**በተጨማሪም ፍትሃዊ እና ተገቢ ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ያመነባቸውን ማንኛውም ሌሎች እፎይታዎች እንዲፈርድ እጠይቃለሁኝ።**

በሐሰት ምስክርነት ቃል ሕግ መሰረት ከላይ የተጠቀሰው እውነተኛ እና ትክክለኛ ስለመሆኑ  አረጋግጣለሁኝ።

*ይሄ ሰነድ ከዩናይትድ ስቴትስ፣ ፖርቶ ሪኮ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ቨርጅን ደሴቶች፣ እና  በዩናይትድ ስቴትስ ግዛት ውስጥ የሚገኙ ማንኛውም ግዛቶች ወይም ቦታዎች ውጪ የሚፈረም ከሆነ፣ ከመፈረሙ በፊት ተጨማሪ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው።*
*ይመልከቱ Super. Ct. Dom. Rel. R. 2(c)(1)(B).*

| | |
|---|---|
| ስምዎን ይፈርሙ በኤሌክትሮኒክስ ለመፈረም በሁለቱም ጎን ላይ /ልክ እንደዚህ/ አግድም ሰረዞችን ያክሉ። | ቀን |
| ስምዎን ያትሙ | ስልክ ቁጥር |
| የመኖሪያ ቤት አድራሻ 1 | ኢሜይል አድራሻ |
| የቤት አድራሻ 2 | |

☐ ተለዋጭ አድራሻ፡- ወከባ እና ጉዳት ይደርስብኛል ብለው በመፍራት የሌላ ሰው አድራሻ ያስገቡ ከሆነ ሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ።